# ክብረ ክህነት

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
፳፻፫ ዓ.ም.

© ማኅበረ ቅዱሳን
፳፻፫ ዓ.ም.

የመጀመሪያ ኅትም ፲፱፻፺፱ዓ.ም
ሁለተኛ ኅትም ፳፻፫ ዓ.ም.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡
All rights reserved.

**ይህ መጽሐፍ**
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
የኤዲቶርያል ቦርድ ታርሞና ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው፡፡

**አድራሻ፡-** በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ፖ.ሳ.ቁ. 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

## መታሰቢያነቷ

ሰማዕትነትን በዘመናችን ላሳዩን በጅማና በኢሊባቡር አውራጃዎች ለቀናችው ሃይማኖት ታምነው በቤተ መቅደሱ ደማቸው ፈስሶ ለካህን የሚገባ ሞት ለሞቱት ቀሳውስትና ማተባችንን አንበጥስም ብለው አንገታቸው ለተበጠሰ ምእመናን ትሁንልኝ!

**ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ**
☎ 251 091 2 08 18 29
✉ 24467 / 1000 አዲስ አበባ
henok_tsehafi@yahoo.com

ለነፍስ አባት የሚሰጠው የሚጠመጠም ሻሽ ብቻ አይደለም መጻሕፍትም እንጂ::

ይህችን መጽሐፍ የምታነቡ አባቶቼ ካህናትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሆይ! ይህችን ጽሑፍ በዓይነ መንፈስ እንደምትመለከቱልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፤ «በሊቃውንት ፊት አትጥቀስ» የሚለውን የኢያሱ ሲራክን መጽሐፍ ቃልም አልዘነጋሁትም:: ይሁንና ከአበው ምንጭ ቀድቼ እንጂ ከራሴ አንቅቼ የጻፍኩት የለምና የጎደለውን ሞልታችሁ የተጣመመውን አቃንታችሁ እንድታነቡልኝ በአክብሮት እማጸናለሁ! በዚህች ጽሑፍ በዓይናችሁ ፊት ሞገስን አግኝቼም እንደሆነ ረድኤተ እግዚአብሔር እንዳይለየኝ በጽንዕት ጸሎታችሁ እንድታስቡኝ እለምናለሁ!!

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

## መግቢያ

ይህ «ክብረ ክህነት» የተሰኘ መጽሐፍ በሰባት ምዕራፎች የተከፈለ ነው:: መጽሐፉ በዓቢይ ርእስነት ክብረ ክህነትን አስመልክቶ የተጻፈ ቢሆንም በውስጡ ግን «ሕይወተ ካህንን» ፤ «ንስሓና ኑዛዜን» የሚመለከቱ ሰፊ ሐሳቦችን ይዟል:: የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት እንደሚከተለው ነው::

የመጀመሪያው ምዕራፍ «ሥልጣነ ክህነት በሐዲስ ኪዳን» የሚል ሲሆን የክህነትን አመሠራረትና መስፋፋት፤ የሐዲስ ኪዳን ክህነት አያስፈልግም ለማለት የሚቀርቡ ተቃውሞዎችና መልሶቻቸው ፤ ክህነት ለማን እንደሚሰጥና ለማን እንደማይሰጥ ከነምክንያቱ፤ እንዲሁም ክህነትን መቀበልን ለሚሹና ለተቀበሉትም ጠቅለል ያለ ትምህርት የቀረበበት ነው::

ሁለተኛው ምዕራፍ «የካህናት ሥልጣን» የሚል ሲሆን በአንብሮተ ዕድ የምትሰጠውን የክህነት ሥልጣን ታላቅ ሹመት ስለመሆንዋ፤ የካህናት ሥልጣን በምን በምን ላይ እንደሆነ ፤ የካህኑ ምግባር በሥልጣኑ ላይ ተጽዕኖ እንዳለውና እንደሌለው በአጠቃላይ ሥልጣንን አስመልክቶ ሰፋ ያለ መረጃ ተቀምጦበታል::

ምዕራፍ ሦስት ደግሞ «የካህናት ጾር» የሚል ነው:: ካህናት ላይ የሚመጣ የዲያቢሎስ ፈተናን በሚመለከት በአራት ንዑሳን አርእስት የተከፈለ ምዕራፍ ነው:: እንደ እግዚአብሔር ፍጥረት ብዙውን እንደ አንድ ቆጥረን እንጂ በካህናት የሚመጣ ፈተና አራት ብቻ ነው ለማለት አይደለም:: እንዲሁም በተለይ በካህናት ላይ የሚጸናውን ብቻ ለማስቀመጥ ተሞክሯል:: በዚህ ምዕራፍ የካህናትን ጾር አስመልክቶ እንደ ማስረጃ የተቀመጡት በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገቡ የቀደሙ አባቶች ናቸው:: ገደብ አልፈን «ዛሬ እንዲህ እየተደረገ ነው...» እያልን የሐሜተኞች ጥቅስ መሆንን አንሻምና!

፬. ትሩፋትን መለማመድ

፭. ክህነትን ለክብር መያዝ

## ምዕራፍ አምስት

## <u>የንስሐ አባት እና የንስሐ ልጅ</u>

(ንስሐና ሥርዓተ ኑዛዜ)

፩. በንስሐ ሒደት የካህኑ ድርሻ

ሀ. መልካም እረኛ መሆን

- ምሕረት መንፈሳዊን በማድረግ
- በርኅራኄ በመገሠጽ
- ስለ ንስሐ ልጆቹ በመጸለይ

ለ. ሳይታክቱ ማስተማር

ሐ. ያለማድላት ሁሉን ማገልገል

- በጾታና በዕድሜ አለመለያየት
- በዘርና በቋንቋ አለመለያየት
- በምግባር አለመለያየት
- በምድራዊ ክብር አለመለያየት

መ. የንስሐ ልጆችን ሕይወት መከታተል

ሠ. ሥርዓት ቤተ ክርስቲያንን ማስከበርና ሳይፈሩ መገሠጽ

፪. በንስሐ ሒደት የምእመናን ድርሻ

ሀ. መምህረ ንስሐ መያዝ

ለ. ኃጢአትን ለካህን መናዘዝ

- የኑዛዜ መጽሐፍ ቅዱሳዊነት
- ለምን ለእግዚአብሔር ብቻ አንናዘዝም?
- ኑዛዜን እንደሚገባ በዝርዝር መፈጸም
- በኑዛዜ ወቅት ተስፋ አለመቁረጥ ስለ ትዕቢትና መዘናጋት
- ኑዛዜና ንጽጽር

ሐ. ቀኖናና መንፈሳዊ ሥርዓት

መ. መምህረ ንስሐ ስለ መምረጥና ስለ መለወጥ



## ምዕራፍ ስድስት

## <u>ለካህናት የሚገባ አክብሮትና አገልግሎት</u>

## ምዕራፍ ሰባት

## <u>ካህናትን መገሠጽና መንቀፍ ከትምህርተ ሃይማኖት አንጻር</u>

በመሆንዋ ነው።

## ክህነት በሁለቱ ኪዳናት

ለቅዱሳን ሐዋርያትና በሥፍራቸው ለሚተኩ ካህናት የተሰጠችው የሐዲስ ኪዳን ክህነት ከቀደመችው የብሉይ ኪዳን ክህነት እጅግ የከበረችና የምትበልጥ ናት። በሥልጣንም የሐዲስ ኪዳን ካህናት የሚበልጥ ሥልጣን አላቸው። መተርጉማን በጸሎተ ኪዳን ላይ «*ዘወሀብከነ ከመ ንፍታሕ ዘኢይትፈታሕ* / የማይፈታውን እንፈታ ዘንድ የሰጠኸን» የሚለውን ሲተረጉሙ «ምድራውያን ነገሥታት የማይፈቱትን እንፈታ ዘንድ ፤ ሌዋውያን ካህናት አያስተሰርዩት የነበረውን ውሳጣዊ ኃጢአት እናስተሰርይ ዘንድ የሰጠኸን» በማለት የሐዲስ ኪዳንን ክህነት ትልቅነት በመመስከር ነው።

ሥልጣነ ክህነት ጌታችንን በመስቀል ከተባበሩ ከሌዋውያን ካህናት ተነጥቆ ለሐዲስ ኪዳን ካህናት ስለመሰጠቱ ጌታችን በምሳሌ ተናግሮአል። ‹‹የወይን አትክልት የተከለ ባለቤት ሰው ነበረ ቅጥርም ቀጠረለት ... ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ። የሚያፈራበት ጊዜ ሲቀርብ ፍሬውን ሊቀበሉ ባሮችን ላከ ፤ እነርሱን ገደሉአቸው። በኋላ ግን ልጄንስ ያፍሩታል ብሎ ልጁን ላከባቸው። ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩ ጊዜ ፡- ወራሹ ይህ ነውና እንግደለውና ርስቱን እናግኝ ተባባሉ። ይዘውም ከወይኑ አትክልት አወጡና ገደሉት። እንግዲህ የወይኑ አትክልት ባለቤት በመጣ ጊዜ ምን ያደርግባቸዋል እነርሱም ፡- ክፉዎችን በክፉ ያጠፉቸዋል <u>የወይኑንም አትክልት ፍሬውን በየጊዜው ለሚያስረክቡ ለሌሎች ገበሬዎች ይሰጠዋል።</u> ›› (ማቴ. ፳፩+፴፫-፵፩) በዚህ ምሳሌ ላይ በነፍሰ ገዳይ ገበሬዎች የተመሰሉት ነቢያትንና ወልደ እግዚአብሔርን የገደሉ የኦሪት ካህናት ናቸው። የወይኑ አትክልት



የተባሉት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሲሆኑ በቀድሞዎቹ ገበሬዎች ተተክተው እንዲጠብቁ የተሾሙት ደግሞ የሐዲስ ኪዳን ካህናት ናቸው።

የሐዲስ ኪዳን ካህናት ከቀደሙት የብሉይ ኪዳን ካህናት ይልቅ የከበሩና ወደ እግዚአብሔር የቀረቡ ናቸው። አበው ይህን በምሳሌ ሲያስረዱ በሰማያውያን መላእክት በመመሰል ነው። በሰማያት ከመንበረ ጸባኦት የቀረቡ ኪሩቤልና ከመንበረ ጸባኦት ርቀው የሚቆሙ ሀያ አራቱ ካህናተ ሰማይ አሉ። ከመንበሩ የራቁት ሃያ አራቱ ሊቃናት የካህናተ ብሊት (የብሉይ ኪዳን ካህናት) ምሳሌ ሲሆኑ ለመንበሩ የቀረቡ ኪሩቤል ደግሞ የካህናተ ሐዳስ (የሐዲስ ኪዳን ካህናት) ምሳሌ ናቸው።

ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ክህነቱ ሲለወጥ ሕጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነውና›› እንዳለ የሐዲስ ኪዳን ክህነት ሕገ ኦሪት ከሕገ ወንጌል የምትበልጠውን ያህል የበለጠ ነው። (ዕብ. ፯+፲፪) የሐዲስ ኪዳን ካህናት የቀደሙት ሌዋውያን ሊገቡበትና ሊያገለግሉበት በማይቻላቸው በቤተ መቅደስና በሐዲስ ኪዳን *መሠዊያ* /ታቦት/ የሚያገለግሉ በመሆናቸው በክብር ይበልጣሉ። ‹‹*መሠዊያ* አለን ከእርሱም ሊበሉ /ከሥጋ ወደሙ/ ድንኳኒቱን የሚያገለግሉ /ሌዋውያን ካህናት/ መብት የላቸውም›› ዕብ. ፲፫+፲

የሀዲስ ኪዳን ክህነት የዘር ሐረግ ተቆጥሮ የሚሰጥ ሳይሆን የቋንቋን የባሕልና የዘርን ገደብነት ተሻግሮ የሚሰጥ ነው። ለሐዲስ ኪዳን ክህነት ብቁ ያልሆነ ቋንቋና ነገድም የለም። ራሱ እግዚአብሔር በትንቢት እንዳጻፈ ‹‹አሕዛብንና ልሳናትን ሁሉ የምሰበስብበት ጊዜ ይደርሳል ፤ እነርሱም ይመጣሉ ፤ ክብሬንም ያያሉ ... ካህናትና ሌዋውያን እንዲሆን ከእነርሱ እወስዳለሁ።›› ኢሳ. ፷፮+፲፰-፳፩

ዕጣን ተቀበልልኝ እጅ መንሣቴም እንደ ሠርክ መሥዋዕት ትሁን» ፤ «ለአንተ የምስጋና መሥዋዕት እሠዋለሁ» ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ «እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።» «የምስጋናን መሥዋዕት ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ በእርሱ እናቅርብለት ፤ ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና » በማለት ለሁላችን ስለተሰጠው መንፈሳዊ ክህነት አስረድቶናል። (መዝ. ፻፵+፪ ፤ መዝ. ፻፲፭+፰ ፤ ሮሜ. ፲፪+፩ ፤ ዕብ. ፲፫+፲፭)

በሌላ በኩል ካህን ማለት ተክህነ ከሚለው ግሥ የወጣ ሲሆን አገልጋይ የሚል ትርጉምም አለው። ስለዚህ «ካህናት ናችሁ» ሲል የነገሥታት ንጉሥ የእግዚአብሔርን ክብር እንድትነግሩ የተመረጣችሁ «አገልጋዮች ናችሁ» የሚል ትርጉምም አለው። *«ያመነ ሁሉ ካህን ነው» የሚለው አባባል ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አያስፈልግም ፤ ምሥጢራትም በየሜዳው መፈጸም አለባቸው ወ.ዘ.ተ የሚሉ የኑፋቄ ሃሳቦችን ያዘለ ነው። ደግሞስ ሁሉ እረኛ ከሆነ መንጋው ማነው?*

ቅዱስ ጳውሎስ «እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን ሁለተኛም ነቢያትን ሦስተኛም አስተማሪዎችን ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ እርዳታንም አገዛዝንም የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጓል። ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ አስተማሪዎች ናቸውን? ሁሉስ ተአምራትን ይሠራሉን? ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን? ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን? ነገር ግን



የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ» (፩ኛ ቆሮ ፲፪+፳፰-፴፩) በማለት የተናገረው ቃል ክህነትም የሁሉም ላለመሆኑ ማስረጃ ነው። ደግሞስ ይኸው ሐዋርያ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ ስለ ካህናት (ስለ ዲያቆናት ፤ ስለ ቀሳውስትና ስለ ኤጲስ ቆጶሳት) አመራረጥ የጻፈላቸው ሁሉም ካህን ቢሆን ነውን? አይደለም። ክህነት ምሥጢር የምትሰኘው አንድም ለተለዩ ሰዎች የምትሰጥ ስለሆነች ነው። ምሥጢር ለቀረቡና ለወዳጆች እንደሚነገር ክህነትም እግዚአብሔር ለመረጣቸው የሚሰጣት ጸጋ ናትና ምሥጢር ትባላለች።

## ሴቶች ለምን አይክኑም?

ክህነት በጸታ ረገድ ለወንዶች ብቻ ይሰጣል። እግዚአብሔር ለወንዶች ብቻ የሰጠው ለሴቶች ያልተሰጠ ፤ ለሴቶች ብቻ የሰጠው ለወንዶች ግን ያልተሰጠ ብዙ ነገር አለ። ክህነት ለሴቶች የማይሰጥ መሆኑን በመጻሕፍት ከቀደመው ዘመን ጀምሮ የሴት ካህን አለመኖሩንና በሐዲስ ኪዳንም ከተመረጡት ሐዋርያት መካከል ሴቶች አለመኖራቸውን በማስረጃነት ማቅረብ ይቻላል። በትርጓሜ ወንጌል በተመዘገበው ምሥጢርም ጌታችን ከሙታን በተነሣ ጊዜ ቀድማ ትንሣኤውን ያየችው ማርያም መግደላዊት ልትነካው ስትል «አትንኪኝ» ማለቱ ሴቶች ሥጋ ወደሙ ለመፈተት የሚያበቃው መዓርገ ክህነት እንደማይሰጣቸው ያስረዳል። (ዮሐ ፳+፲፯) በዘመነ ሐዋርያትም ስለ ሴት ካህን የተጻፈ ነገር አይገኝም።

ከዚህም ባሻገር ግን እግዚአብሔር ሙሴን ለመንግሥት አሮንን ለክህነት ለምን እንደመረጠ እንደማይታወቅ ሁሉ ወንዶችን ብቻ ለምን ለክህነት እንደመረጠ የሚያውቀው እርሱ ባለቤቱ ነው። ምናልባትም አሁን በድንግዝግዝ እንደምናይ ነንና ባለንበት በሥጋዊ አእምሮ የማንረዳው ኋላ በአጸደ ነፍስ ወይም ከዚህ በተለየ አቅዋም ሆነን ልንረዳው የምንችል ረቂቅ ፍርዱ ነው ብለን ልናልፈውም እንችላለን።

የተቀበሉት የምዕራቡን ፤ በደቡብ የተቀበሉት የሰሜኑን እያበላለጡ ክህነትን ማቃለል የሰዎች ደካማ አስተሳሰብ እንጂ ምንም ዓይነት ትውፊታዊ መሠረት የለውም።

በዘመነ ኦሪት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር በሙሴ አማካይነት ይገናኝና ይነጋገር ነበር። ታዲያ በአንድ ወቅት ሙሴ ሰባ ሽማግሌዎችን ሰበሰበ የእግዚአብሔርንም ቃል ነገራቸው። እግዚአብሔርም በደመናው ወርዶ ተናገረው በሙሴም ላይ ከነበረው መንፈስ ወስዶ በሽማግሌዎቹ ላይ አደረገ። መንፈሱም በላያቸው ባደረ ጊዜ ትንቢትን አንድ ጊዜ ብቻ ተናገሩ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ከሕዝቡ መካከል በሰፈር የቀሩ ኤልዳድና ሞዳድ የሚባሉ ሰዎች ነበሩ። መንፈስ ወርዶባቸው በሠፈር ሳሉ ትንቢት ተናገሩ። አንድ ጎበዝ ሰው እየሮጠ መጥቶ ፡- ኤልዳድና ሞዳድ በሰፈር ትንቢት ይናገራሉ» ብሎ ለሙሴ ነገረው። ከልጅነቱ ጀምሮ የሙሴ አገልጋይ የነበረው የነዌ ልጅ ኢያሱ፡- «ጌታዬ ሙሴ ሆይ ከልክላቸው» አለው። ሙሴም፡- «የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ መንፈሱን ቢያወርድ አንተ ስለእኔ ትቀናለህን?» አለው። (ዘኁ ፲፩+፳፬ ፥ ፴)

ይህን ታሪክ ከክህነት ጋር በተያያዘ ብንመለከተው ብዙ ቁም ነገርን ልናነሣበት እንችላለን። እርሱ ክህነት ተቀብሎ ሌሎች ክህነት ሲቀበሉ ዓይኑ ደም የሚለብስ ፤ ክህነትን የሚቀበሉ በበዙ ቁጥር ፈቃደ እግዚአብሔርን ሳያስተውል ዘመኑ እንደተበላሸ አድርጎ የሚቆጥር ፤ እርሱ ክህነትን ከተቀበለ በኋላ የተቀበሉ ሁሉ ክህነታቸው ክህነት እንዳልሆነ አድርጎ የሚያስብ አንዳንድ ሰው ይኖራል። ይህ ዓይነቱ ሰው ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የነገ ህልውና የማያስብ ነው። የሚያስብ



ቢሆን ምእመናን ሁሉ ተምረው ካህናት ቢሆኑ እግዚአብሔር ካልከለከላቸው እርሱ ምን ቸገረው? ደግሞስ የቱንስ ያህል «አይገባውም» የተባለ ሰው ቢቀበላት ቅድስቲቱ ክህነት ትረክሳለችን? አትረክስም።

በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የተቀመጠውን መሥፈርት እስካሟላ ድረስ ማንኛውንም ምእመን ከክህነት የሚያግደው ነገር የለም። አፍአዊ ገጽታ ፤ ባዕለጸግነት ፤ ከተሜነት ወ.ዘ.ተ. ብዙዎች እንደሚገምቱት ከክህነት አያግድም። ግልጽ ለማድረግ ያህል አንዳንድ ጊዜ ውጪአዊ ገጽታን ብቻ በመመልከት እና ሰውን በመልክዓ ነፍሱ (በነፍሱ መልክ) ባለማየት ለክህነት እንደማይሆን የሚያስቡ ይኖራሉ። አንዳንዶች ደግሞ ምድራዊ ባዕለጸግነት ያለው ወይም የባዕለጸጎች ልጅ ክህነት ቢቀበል ዝቅ እንደሚል የሚያስቡና *«አንተማ የትልቅ ሰው ልጅ ነህ...!»* ብለው የሚያከለክሉ የገንዘብ አምላኪዎች ፤ ልጃቸውን የሚከለክሉና በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንደ ከፉ ነገር *«ቄስ ሆነህ ልትቀር!?»* የሚሉ ይኖራሉ። ነገር ግን የክህነትን ክብር አለማወቃቸው እንጂ ልጅን ለክህነት ማድረስ ራሱ መንፈሳዊ ዋጋ አለው። «ልጃቸውን አስተምረው ለክህነት የሚያበቁ ንጹሕ *መሥዋዕትን* እንዳቀረቡ ይቆጠርላቸዋል።» /ተአምረ ኢየሱስ/

በሌላ በኩል ደግሞ የከተማ ልጅ ፤ ጸዳ ያለ ልብስ የለበሰ ወጣት ለክህነት የሚሆን የማይመስላቸውም አሉ። እርግጥ ነው ይህ አስተሳሰብ ያለ ምንም ምክንያት የመጣ አይደለም። በከተማ ከሚታየው ሥርዓት የለሽ የወጣቶች ሕይወት በመነሣት *«ተቀብሎ አክብሮ አይዘው ይሆን?»* ከሚል ሥጋት የመነጨም ነው። ይሁንና የከተማ ልጅ የሆነ ሁሉ ክህነትን ጠብቆ አይይዝም ብሎ መደምደም አይቻልም። ገጠር ተወልደና አድጎም መሬት የማይበቃውም አለ። ሰውን ከኃጢአት

የሚከለክለው የከተማ ወይም የገጠር ልጅ መሆኑ ሳይሆን እግዚአብሔርን መፍራቱ ነው።



ምዕራፍ ሁለት

# የካህናት ሥልጣን

## እጅግ የከበረ ሥልጣን

የሐዲስ ኪዳን ሥልጣነ ክህነት በሥጋና በነፍስ በሰማይና በምድር ፤ በሰውና በመላእክት ላይ ነውና እጅግ የከበረ ደገኛ ሥልጣን ነው። የክህነት ሥልጣን ከሥልጣናት ሁሉ ከፍ ያለች ናት። ሌላው ቀርቶ የክህነት ሥልጣን ንጉሥ ሥልጣን ይበልጣል። ምክንያቱም ነገሥታት ሥጋን ለመጠበቅና ለማስተዳደር የሚሾሙ ሲሆን ካህናት ግን በእግዚአብሔር የሚሾሙት ሥጋንና ነፍስን ከጥፋት ይጠብቁ ዘንድ ነው።

ነፍስ ከሥጋ የሚበልጠውን ያህል ክህነት ከመንግሥት ይበልጣል። ፍትሐ ነገሥት «በከመ ነፍስ ትከብር እምሥጋ ከማሁ ክህነትኒ ትትሌዓል በክብር እመንግሥት /ነፍስ ከሥጋ እንደምትበልጥ እንደዚሁ ክህነት በክብር ከመንግሥት ትበልጣለች።» (ፍት.ነገ.መን. ፱፥፪) ሥጋ በዚህች ምድር ፈርሳና በስብሳ የምትቀርና በሌላ አካል የምትተካ ስትሆን ነፍስ ግን በዚህች ምድርም በወዲያኛውም ዓለም የምትኖር ሕያዊት ናት። የመንግሥትነት ሥልጣንም በዚህች ምድር ሽረት ባይገኝም እንኳን በኀልፈት /በሞት/ የሚገታ ነው። የክህነት ሥልጣን ግን በወዲያኛውም ዓለም የማያቋርጥ ነው።

ሥልጣነ ክህነት [5]የጸጋ አምላክነት ሲሆን ካህናትም የጸጋ

[5] አምላክ የሚለው ቃል ‹መለከ› ገዛ ከሚለው ግሥ የተገኘ ሲሆን ገዥ የሚል ትርጉም አለው። እግዚአብሔር በባሕርይው ፈጥሮ የሚገዛ ጌታ ሲሆን

ምንም ሥራቸው ባያምር የሚሉትን አድርጉ ከተባለ ለከበሩት ለሐዲስ ኪዳን ካህናትማ ይልቅ መታዘዝና ምግባራቸውን አለመመልከት እንዴት ይገባ ይሆን?

ካህናት ኃጢአትን ቢሠሩም ሁሉም እንደ ሥራው ይቀበላልና እነርሱን ሰበብ አድርጎ ከመንፈሳዊ ሕይወትም ሆነ ከካህናት መሸሽ አይገባም:: የራስን ኃጢአት ማሰብ እንጂ! ፤ በገላ ፮፥፬ ላይ- «ሰው ሁሉ ለሌላው ያይደለ ለራሱ ክብር በሚሆነው ገንዘብ ሥራውን ይመርምር ፤ ሁሉም እንደ ሥራው ፍዳውን ይቀበላልና» ተብሎ ተጽፎአል:: ከዚህ ቃል ትርጓሜ ጋር የሚከተለው ታሪክ ተጽፎአል:-

አንድ ባለጸጋ ምእመን ገበሬ ነበረው:: ይህን ገበሬ *«ሂድና የንስሓ አባቴን ርስት እረስ ብሎ»* ይልከዋል:: ይህም ገበሬ ከመምህረ ንስሓው ርስት ሆኖ ሲያርስ ድስት ሙሉ ወርቅ ያገኝና ሄዶ ለባለጸጋው ይነግረዋል:: እርሱም *«ለእኔ ለምን ነገርኸኝ እኛማ ርስቱን ማረሳችን ፍሬ አፍሰን ልንበላ ነው? ወርቅ ለባለ ርስት ነው! ለእርሱ ንገረው ነገር ግን ነገርሁት አትበል ይጣላሃል»* አለው:: ሄዶ ነገረው ያም ቄስ *«የምናወጣበትን ስታሰናዳ ቆየኝ»* ብሎ እርሱን ሰዶ ሰይፉን ሲስል አመሸ:: ሔደው ቆፍረው ወርቁን ካወጡ በኋላ አንገቱን በሰይፍ ብሎ ገድሎታል:: ወርቁም ደም ተፈንጥቆ ቢያርፍበት ብረት ሆኗል:: ያ ሰውም (ባለጸጋው) ከአሁን አሁን ይመጣል እያለ ቢጠብቅ ቀረ:: ምን ሆኖ ይሆን እያለ እየፈለገ ሲሄድ ዐሠረ ደም (የደም ምልክት) አገኘ:: *«ያ ከፉ ተጣልቶታል ለጣላው?»* ብሎ አሰበ:: መልሶ «ምን ዕዳዬ! አንተም አንድ ጊዜ ብጹዓን አግብርት (ካህናት) ከተባሉት ተቆጥረሃል:: እኔም ከእንግዲህ በቄስ እጅ ሥጋ ወደሙን አልቀበልም ቤተ እግዚአብሔርም አልገባም» ብሎ ተከለከለ::



በኋላ መልአክ የምታየው ነገር አለና ወደ ቤተ እግዚአብሔር ውጣ አለው ፣ ወጣ:: ሰይጣን በዚያ ቄስ እጅ ላይ ሆኖ በእሳት ልጓም ለጉሞ በእሳት አለንጋ እየገረፈ ይዞት ሲመጣ አየ:: ካህኑ ከቤተ እግዚአብሔር ሲገባ ሰይጣኑ ሲወርድለት ሥራውን ሠርቶ ሲወጣ እንደቀደመው በላይ ላይ ሆኖ በእሳት ልጓም ለጉሞ በእሳት አለንጋ እየገረፈ ይዞት ሲሄድ አይቶ «ለካስ ቅዱስ ጳውሎስ ሁሉም የራሱን ሸክም ይሸከማል ያለው ለዚህ ነው::» ብሏል ፤ ዳግመኛም የወርቅ ገደል (ውኃው የሚያርፍበት ወርቅ ፤ ማንኪያው የወርቅ ሆኖ ፤ አንድ እጁ እግሩ የቆሰለ ድውይ በማንኪያው እየጩለፈ እንካ ጠጣ ሲለው ተጸይፎ አልጠጣም ሲል ፤ *«ምነዋ ላይ ታቹ የወርቅ ማንኪያው የወርቅ ጠጣ እንጂ»* ሲለው ተመልክቶአል:: «የቄሱን አትመልከት ሥጋውን ደሙን ተቀበል ሲለኝ ነው» ብሎ ተጸጽቶ ሥጋውን ደሙን የሚቀበል ሆኗል:: ይላል:: ከዚህ ታሪክ እንደምንረዳው ካህናትን ሰበብ አድርጎ ከመንፈሳዊ ጸጋ መለየት አለማስተዋል ነው::

ይልቁን በካህናት ዘንድ የጎላ የምግባር ሕጸጽ (ጉድለት) ሲታይ ምእመናን ስለ ኃጢአታችን ነው ብለው ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩ ይገባል ፤ *«ወኢይጽአሉ ሕዝብ ከኢራን እለ ውጹአን እምኔነ /የማያምኑ የእንግዳ ወገን (የመናፍቃን ፤ የአለማውያን) መዘባበቻ አታድርገን»* እያሉ ሊያለቅሱ ይገባል::

ቤተ ክርስቲያን «በእንተ ቅዱሳት» በተሰኘው ጸሎት ላይ ሕዝበ ክርስቲያኑ በእግዚአብሔር ፊት በግንባሩ ተደፍቶ ለጳጳሳት ለቀሳውስትና ለዲያቆናት ዕድሜ እንዲሰጣቸው ፤ ፈሪሀ እግዚአብሔርን እንዲያሳድርባቸው እና ድካመ ነፍሳቸውን አቅልሎ በቅድስና ይቀርቡ ዘንድ እንዲያተጋቸው እንዲለምን የምታደርገው ለዚህ ነው::

### ምዕራፍ ሦስት

# የካህናት ጾር /ፈተና/

አባቶች ካህናት በሯቱ አእማደ ምሥጢር ካመኑ ከሯቱ ጾታ ምእመናን (የምእመናን ወገን) ውስጥ የሚመደቡ እንደመሆናቸው በእነርሱም ላይ እንደማንኛውም አማኒ ጾር (ፈተና) አለባቸው:: ማንኛ ውም ምእመን ተፈትኖ እንደሚወድቅ ሊወድቁ ፤ እንደማይወድቅ ሳይወድቁ ይችላሉ:: ምንም በክብር ከፍ ያሉ ቢሆኑም ለእነርሱ ተለይቶ የተሰጣቸው ጾር ማጥፊያ የለም ፤ እነርሱም ዲያብሎስን ድል ሊነሡ የሚችሉት እንደማንኛውም ምእመን በጥምቀት ባገኙት ኃይል ነው:: ስለዚህ ካህን ቢወድቅ ያልተለመደ ክስተት አይደለም::

አንዳንድ ሰዎች *«ካህናት ከቤተ መቅደስ ሳይለዩ በእግዚአብሔር ፊት እያገለገሉ እንዴት ሰይጣን ሊፈትናቸው ይችላል?»* ብለው ይጠይቃሉ:: ይሁንና ይህ ሃሳብ ልክ አይደለም:: ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን በገዳመ ቆሮንቶስ ከጾመ በኋላ በዲያብሎስ በተፈተነ ጊዜ ዲያብሎስ በምድረ በዳ ከፈተነው በኋላ ወደ ቤተ መቅደስ የሄደለት «ካህናትን ድል በምነሳበት በቤተ መቅደስ ቢሆን መች ድል ይነሣኝ ነበር» የሚል ሃሳቡን ስለተረዳ ነው:: (ማቴ ፬+፭ ትር.) ስለዚህ ዲያብሎስ ካህናትን ድል ሊነሣ የሚችልበት ስፍራ ቤተ መቅደስም ጭምር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል::

ካህናት የሚጸናባቸው ጾር (የሚፈተኑበት ፈተና) ትዕቢት እንደሆነ መጻሕፍት ያስረዳሉ:: «ካህን እም ኢተምሀረ እምኢመጽአ ትዕቢት» «ካህን ባልተማረ ኖሮ ትዕቢት ባልመጣበት ነበር» እንዲል



(ስንክሳር) ዕውቀት ካህንን ወደ ትዕቢት ሊገፋፉ ይችላል:: ይህም አእምሮአችን (እውቀታችን) ረቂቅ ፤ ማዕረጋችን ምጡቅ እያሉ ይታበያሉና ሲል ነው:: እርግጥ ነው ካህናት የሚያውቁት መለኮታዊ ምሥጢር ረቂቅ ነው ፤ ማዕረጋቸው ከመዐርጋት የበለጠ ምጡቅ ነው:: ነገር ግን ለትዕቢት አይደለም:: በክብራቸው ቢታበዩም ከክብራቸው ይዋረዳሉ (ያዕ.፬፥፮) ካህናት በትዕቢት ጾር ይፈተናሉ ሲባል ሌላ ጾር አይመጣባቸውም ማለት አይደለም:: ሰይጣን በአንዱ ጾር ድል ሲነሱት በሌላ ጾር መፈተኑን አይተውም ነገር ግን የሚጸናባቸውን ለመናገር ነው::

ከዚህ በመቀጠል የተዘረዘሩት የካህናት ጾር ተብለው የተቀመጡት ሀሳቦች ከትዕቢት የሚመጡ ናቸው:: ትዕቢት የፈሪሐ እግዚአብሔርን መጉደል ያመጣል:: ፈሪሐ እግዚአብሔር ሲጎድል ደግሞ ከዚህ በታች እንደተዘረዘሩት ያሉ ግብሮች ከመፈፀም ያደርሳል::

## ፩ ፍቅረ ነዋይ

ፍቅረ ነዋይ ከትዕቢት ጋር የሚተካከል ሌላ ጾር ነው:: ካህናትን በትዕቢት የሚፈትን ዲያብሎስ በፍቅረ ነዋይም ይፈትናቸዋል:: ፍቅረ ነዋይ ማለት በቁሙ ገንዘብን መውደድ የሚል ትርጓሜ ሲኖረው በመንፈሳዊ አተረጓጎም ግን ከገንዘብ ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም:: ልብ የሚቆምለት የሚመኙት ነገርን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው:: *«ኢይምሰልከ አ ፍቁር ከመ አጥርዮ ወርቅ ወብሩር ውእቱ ባሕቲቱ ፍቅረ ጥሪት አላ ኵሉ ዘይሰቀል ቦቱ ፍትወታቲከ* / ወዳጄ ሆይ ወርቅና ብርን ማከማቸት ብቻ ገንዘብን መውደድ አይምሰልህ ምኞትህ የሚሰቀልለት ነገር ሁሉ ነው እንጂ» እንዲል (ማር ይስሐቅ)